# የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ወይስ የመንፈስ?

ከተስፋዬ ሮበሌ

ይህ ወንድም ተስፋዬ ሮበሌ፣ *"በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ! የአስተምህሮተ ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ ትንታኔ"* በሚል ርእስ ካዘጋጀው መጽሐፍ፣ ከምዕራፍ ሰባት በቀጥታ የተወሰደ ነው። በሙታን ትንሣኤ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ይህን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታለን።

ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁዳውያን ተሰቅሎ አልተገደለም ስለዚህ ከሞት ተነሥቶአል የሚለው ጉዳይ ያልሞተን ሰው ከሞት ተነሥቶአል ማለት ስለሆነ ስሕተት ነው የሚል አቋም እንዳላቸው ሁሉ፣ ለዘብተኛ አቋም ያላቸው የነገረ መለኮት ምሁራን ደግሞ፣ "ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶአል"፣ "መቃብሩ ባዶ ነው"፣ "ኢየሱስ ከሞት ካልተነሣ አስክሬኑ እንዴት አልተገኘም?"፣ "ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉ በርካታ ጥንታዊ ሰነዶች መነሣቱን እንዴት ሊመሰክሩ ቻሉ?" ወዘተ የሚሉትን ማስረጃዎች ወደ ጐን በመተው፣ ላለመነሣቱ እንዲሁም መቃብሩ ባዶ ላለመሆኑ በርካታ መላምቶችን እንደሚያቀርቡ ተመልክተናል። ዋና ዋና ለሚባሉትም መላምቶች ተጨባጭ መከላከያ ለማቅረብ ሞክረናል። መናፍቃዊ የሆኑ ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ እናምናለን ይበሉ እንጂ፣ ትንሣኤው ግዘፋዊ/ቊሳዊ ሳይሆን በመንፈስ ነው የሚል አቋም አላቸው። ከላይ ባየናቸው ምዕራፎች፣ መቃብሩ ባዶ ነው፣ ደቀ መዛሙርቱም የትንሣኤውን ጌታ በዐይነ ሥጋቸው አይተውታል ወዘተ በሚል ያቀርብናቸው እጅግ በርካታ ማስረጃዎች ትንሣኤው በመንፈስ ሳይሆን በአካል መሆኑን በግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው። ይህ በሆነበት ሁኔታ፣ መናፍቃን በተለይ ደግሞ የይሖዋ ምስክሮች ቃለ እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን፣ ታሪክ ራሱ ርእሱ ጉዳዩን በግልጽና በስፋት የሚያስተምርበት ሁኔታ እያለ ትንሣኤው የመንፈስ ነው ማለታቸው ስሕተት ነው። ከዚህ በመቀጠል ይህን ጉዳይ በስፋት ለመመርመር እንሞክራለን።

"ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ወይስ የመንፈስ?" የሚለው ርእስ ጉዳይ ለትንሣኤ ሙታን አስተምህሮ እጅግ መሠረታዊው ትምህርት ነው። ርእስ ጉዳዩን በጥልቀት መመርመር ይቻለን ዘንድ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ትንሣኤ ሙታንን አስመልክቶ የቀረቡትንና ሊቀርቡ የሚችሉትን አማራጭ ትንተናዎች ከተመለከትን በኋላ ትንሣኤው የአካል ነው ወይስ የመንፈስ የሚለውን ጉዳይ በስፋት እንመረምራለን፡—

፩ **አካለ ተንሥአት**[1]**፡—** ይህ ንድፈ ሐሳብ የኢየሱስ ሞት አካላዊ ሞት እንደ ሞተ፣ አካላዊ በሆነ ሁኔታም ከሙታን እንደ ተነሣ ያምናል። ከዚህም የተነሣ የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ባዶ እንደ ሆነ ይቀበላል። የኢየሱስ ክርስቶስ የቅድመ ትንሣኤ ግብረ

---

[1] አካለ ተንሥአት (Bodily Resuscitation)፣ አካለ ትንሣኤ/ተሐድሶ (Bodily Transformation)፣ የመንፈስ ትንሣኤ (Spiritual Resurrection)፣ ምናባዊ ትንሣኤ ንድፈ ሐሳብ (Reductive Resurrection Theories)። የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በተመለከተ የሚሰጡትን ንድፈ ሐሳቦች በዚህ መልክ ያብራሩት የሃይማኖት ፍልስፍና ምሁሩ ፕሮፌሰር ስቲቨን ዳቪስ ቢሆኑም መጽሐፉ ጸሓፊ የመንፈስ ትንሣኤ የሚለውን ጉዳይ ከኢትዮጵያውን ካሉበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ለማብራራት ሙከራ አድርጓል። Stephen T. Davis, *Risen Indeed: Making Sense of the Resurrection* (Grand Rapids: Eerdmans, 1993), 44-45. Stephen T. Davis, *Christian Philosophical Theology* (London: Oxford University Press, 2006), 112-113.

አካል[2] አንዳችም ለውጥ ወይም ተሐድሶ ሳይካሄድበት እርሱ ራሱ ከሙታን ተነሥቶአል። ስለዚህ ትንሣኤው የቆመውን ሕይወት ቀጣይ ከማድረግ ውጪ አንዳችም ተሐድሶ አላመጣም የሚል አመለካከት ነው።

፪ **አካለ ትንሣኤ/ተሐድሶ:—** ይህ ንድፈ ሐሳብ የኢየሱስ ሞት አካላዊ ሞት እንደ ሞተና አካላዊ በሆነ ሁኔታ ከሙታን እንደ ተነሣ ያምናል። ከዚህም የተነሣ የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ባዶ እንደ ሆነ ይቀበላል። የኢየሱስ ክርስቶስ የቅድመ ትንሣኤ ግብረ አካል ቍሳዊ ቢሆንም እንኳ፣ ተሐድሶ ስለተደረገበት፣ "የከበረ አካል" ሆኖ እርሱ ራሱ ከሙታን ተነሥቶአል። የትንሣኤው አካል፣ በቅድመ ትንሣኤ የነበረው አካል ይታይበት የነበረው ተፈጥሮአዊ ባሕርይ አይታይበትም (ለምሳሌ:— መድከም፣ ማርጀት፣ መሞት)።

፫ **የመንፈስ ትንሣኤ:—** ይህ ንድፈ ሐሳብ ደግሞ፣ ኢየሱስ በእውነት እንደ ሞተ የሚቀበል ቢሆንም፣ ከትንሣኤው በኋላ ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሰው አልሆነም፤ እንደ መላእክ መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። ባልታወቀ ምክንያት መቃብሩ ባዶ ቢሆንም[3] ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ እንጂ፣ በአካለ ሥጋ ከሙታን አልተነሣም። ስለዚህ በሞተው ኢየሱስና በተነሣው ኢየሱስ መካከል የነፍስ ወይም የመንፈስ ወይም ደግሞ የአካል አንድነት የለም[4]። እንደዚህ አመለካከት በሞተው ኢየሱስና በተነሣው ኢየሱስ መካከል ያለው አንድነትም ሆነ ልዩነት በውል አይታወቅም። ይህ ዐይነቱ አመለካከት ያላቸው የይሖዋ ምስክሮችና "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅታቸው ነው። እንደ ይሖዋ ምስክሮች ትምህርት የሞተው ኢየሱስ ሰው ሲሆን፣ ከሙታን የተነሣው ደግሞ ሊቀ መላእክ ሚካኤል ነው። እንደ ድርጅቱ ትምህርት፣ በኢየሱስ ሰብአዊ ሕይወት ውስጥ ሊቀ መላእክ ሚካኤል ያልነበረ ሲሆን፣ ከትንሣኤው በኋላ ግን፣ ኢየሱስ ሊቀ መላእክ ሚካኤል ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። እንዲያውም ድርጅቱ ኢየሱስ በምድር ላይ ለሰላሳ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ ይሖዋ አምላክን በትጋት ስላገለገለ፣ ይሖዋ አምላክ ለሚካኤል ያለመሞትን (ኢመዋቲነትን) ሸልሞታል የሚል ትምህርት አለው። ነገር ግን ኢየሱስ ሚካኤል ካልነበረ ወይም በኢየሱስ ውስጥ ሚካኤልነት ከሌለ፣ ኢየሱስ የሚባለው ግለሰብ ሰላሳ ሦስት ዓመት ከመንፈቅ አምላክን አገልግሎ ሳለ፣ በእርሱ ፈንታ ሚካኤል ኢመዋቲነትን በአምላክ እንዴት ሊሸለም ቻለ ለሚለው ጥያቄ ድርጅቱ የሚሰጠው አንዳችም ማብራሪያ የለም።

፬ **ምናባዊ ትንሣኤ ንድፈ ሐሳብ:—** ይህ ንድፈ ሐሳብ ኢየሱስ በትክክል እንደ ሞተና በትክክል ከሙታን እንደ ተነሣ አያምንም። ስለዚህ መቃብሩ ባዶ ነበር ወይስ አልነበረም የሚለው ጕዳይ ከርእሰ ጕዳዩ ጋር ተያያዥነት የለውም ባይ ነው። በትክክል ያልሞተ ነገር ከሙታን ተነሥቶአል ማለት ትርጕም ስለሌለው። ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቶአል የሚባለው ጕዳይ ሊተነተን የሚችለው/የሚገባው ሥነ ልቡናዊ በሆነ መልኩ ነው። ይኸውም በደቀ መዛሙርቱ በነበራቸው ውስጣዊ የአእምሮ ሁኔታ ነው። ኢየሱስ ታየን ወይም ተገለጠልን የሚለው የደቀ መዛሙርቱ ዐዋጅ፣ ራእያዊ አልያም ቅዥት

---

[2] Physiology የሚለውን እንግሊዝኛ ቃል እንዲወክል ታስቦ የተቀመረ ቃል ነው።

[3] የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀውን የይሖዋ ምስክሮች ድርጅት የመሠረተው "መጋቢ" ቻርልስ ታዝ ራሰል፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ መታሰቢያነት አንድ ስፍራ ተጠብቆ ነው ያለው" የሚል ግምት አለው።

[4] እንደ "የይሖዋ ምስክሮች" እንዲሁም እንደ አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሰው ነፍስና መንፈስ ያለው ቍሳዊና መንፈሳዊ ክፍል ያለው ፍጡር አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ነፍስ/መንፈስ እንዲሁም አካል የሚለውን ነገር መጠቀሙ እነዚህ ገለጻዎች ሰው የተለያየ ነገር ባለቤት መሆኑን አያመለክትም የሚል አቋም አላቸው።

(hallucination) ነው። እንደዚህ አመለካከት “ኢየሱስ ከሞት ተነሥቶአል” ማለት “የክርስቶስ መስቀል የማዳን ኀይል አለው” ወይም የእምነቴ ማዕከል ኢየሱስ ነው ከማለት ውጪ አንዳችም ትርጒም የለውም። ይህ ማለት ደግሞ ኢየሱስ ከሙታን ተነሥቶአል የሚለው ጒዳይ የሚብራራው መንፈሳዊ የሆነ ትርጒም ተሰጥቶት እንጂ፣ በቀጥታ ትርጒሙ አይደለም። በአጠቃላይ እንደዚህ አመለካከት የሞተ ሰው ከሙታን ተነሥቶአል የሚለውን ጒዳይ አይቀበልም[5]።

***አካለ ትንሥኤት ንድፈ ሐሳብ*** መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አስተምህሮ ያለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ይህን አስተምህሮ የሚደግፍ አንዳችም ምሁር እንዲሁም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ የለም[6]። የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ፣ ይህ ንድፈ ሐሳብ እንደሚያስተምረው ትምህርት ከሆነ፣ ክርስቶስ ዳግም የመሞት ዕጣ ፈንታ አለው። ነገር ግን ቃለ እግዚአብሔር የኢየሱስ የትንሣኤ አካል እንደማይሞት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (1ቆሮንቶስ 15÷54-55፤ ዕብራውያን 2÷14)። አካለ ትንሥኤት ንድፈ ሐሳብ ትምህርት ከሙታን ተነሥተው ዳግም እንደ ሞቱት ሰዎች (እንደ አልዓዛር፣ እንደ ኢያሪኦስ ልጅ፣ እንዲሁም በናይን ትኖር እንደ ነበረው መበለት) እንጂ፣ በከበረ ሁኔታ ለአንዴና ለዘላለም ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያመለክት አይደለም (ክርስቶስ ዳግም አይሞትምና)። በአጠቃላይ የአካል ትንሣኤ አስተምህሮና አካለ ትንሥኤት ንድፈ ሐሳብ የትንሣኤው አካል ቊሳዊ ነው በሚለው ጒዳይ ላይ ተመሳሳይ አቋም ቢጋሩም፣ የትንሣኤ አካል እንደ ቅድመ ትንሣኤ አካል ሟች ነው የሚለውን የአካለ ትንሥኤትን ንድፈ ሐሳብ አስተምህሮ፣ የአካል ትንሣኤ ትምህርት አይቀበልም[7]።

***ትንሣኤው መንፈሳዊ ነው*** በሚለው አቋማቸው በስፋት የሚታወቁት የይሖዋ ምስክሮች ሲሆኑ፣ ድርጅታቸው አስተምህሮውን ለመደገፍ ያሚያቀርባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች አንድ በአንድ እየነቀስን በማውጣት፣ የክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ሳይሆን የመንፈስ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ሊያደርሱ ይችላሉን የሚለውን ጒዳይ በስፋት ለመመርመር ሙከራ እናደርጋለን።

***ይ***ህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ትንሣኤ ነው፣ የሚለው አስተምህሮ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመት ስታስተምረው የነበረና አሁንም በማስተማር ላይ የምትገኘው ትምህርት መሆኑን ቃለ እግዚአብሔርን፣ ታሪክንና ሥነ አመክንዮን በመጥቀስ ሰፊ ትንታኔ ለማቅረብ ጥረት ያደርጋል።

***የ***አካል ትንሣኤ አስተምህሮ የሚከተሉትን ሁለት መሠረተ ነጥቦች ማዕከል ያደረገ ትምህርት ነው። (1) በሞተው ሰውና ከሙታን በተነሣው ሰው መካከል ልዩነት የለም። ከሞት የሚነሣው የሞተው ሰው ራሱ ነው (የሞተው አካል ከሞት የሚነሣው አካል አያቋርጤ ነው)። ለምሳሌ:— ኢየሱስ ከትንሣኤውም በኋላ ራሱን፣ “እኔው ራሴው ነኝ” (ሉቃስ 24÷39) ብሏል። አስታውሴው፣ ጠባዩ፣ አካላዊ ቅርጹ (ለምሳሌ ከትንሣኤ በፊት በአካሉ ላይ የነበረው ጠባሳ/ዕትራት ከትንሣኤውም በኋላ አብሮት ነበር) ወዘተ አልተቀየረም። (2) ቅድመ ትንሣኤና ድኅረ ትንሣኤ ያለው አካል ቊሳዊ ይዘቱም ሆነ አያቋርጤነቱን በጠበቀ መልኩ ዕድሳት ይደረግለታል

[5] “ትንሣኤውን ለሚቃረኑ መላምቶች አጥጋቢ ምላሽ አለን?” በሚለው ርእስ ሥር ለዚህ ዐይነቱ አተያይ ሰፊ ምላሽ ለመስጠት ሞክረናል።

[6] Stephen T. Davis, *Risen Indeed: Making Sense of the Resurrection* (Grand Rapids: Eerdmans, 1993), 46.

[7] “ትንሣኤውን ለሚቃረኑ መላምቶች አጥጋቢ ምላሽ አለን?” በሚለው ርእስ ሥር ለዚህ አመለካከት ሰፊ ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል።

(ለምሳሌ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሮሜ 8÷11፤ 1ቆሮንቶስ 15÷53፤ ፊልጵስዩስ 3÷20-21)። "አንተ ሞኝ የምትዘራው ካልሞተ ሕይወት አያገኝም። የምትዘራውም የስንዴ ወይም የሌላ ዐይነት ዘር ቅንጣት ብቻ እንጂ ወደ ፊት የምታገኘውን አካል አይደለም። እግዚአብሔር ግን እንደ ፈቀደ አካልን ይሰጠዋል፤ ለእያንዳንዱም የዘር ዐይነት የራሱን አካል ይሰጠዋል" (1ቆሮንቶስ 15÷36-38)፣ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል የስንዴን ቅንጣት በመውሰድ የሚያስተምረው ትምህርት፣ ቅድመ ትንሣኤና ድኅረ ትንሣኤ አካል ቀኣሳዊ አያቋርጤነት እንዳለው የተዘራውን ዐይነት ዘር ከተዘራው ዘር ላይ እንደሚበቅል ነው። አንዱ በሌላው እንደሚተካ ወይም አንዱ በሌላው እንደሚቀየር ሳይሆን፣ ይኸው አካል በትንሣኤ ሂደት ውስጥ እንደሚታደስ ነው። ቅድመ ትንሣኤ አካል ይበሰብሳል፣ ይሞታል፣ ክብር የሌለው እንዲሁም ፍጥረታዊ ሲሆን ድኅረ ትንሣኤ አካል ግን የማይበሰብስ፣ ክብርንና ኀይልን የተሞላ እንዲሁም መንፈሳዊ ነው (1ቆሮንቶስ 15÷42-44)።

| ቅድመ ትንሣኤ አካል | ድኅረ ትንሣኤ አካል |
|---|---|
| የሚበሰብስ አካል<br>φθορᾷ, | የማይበሰብስ አካል<br>ἀφθαρσίᾳ· |
| የተዋረደ<br>ἀτιμίᾳ | የከበረ<br>δόξῃ |
| ደካማ<br>ἀσθενείᾳ | ኀያል<br>δυνάμει |
| ፍጥረታዊ አካል<br>σῶμα ψυχικόν | መንፈሳዊ አካል[8]<br>σῶμα πνευματικόν |

## "በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ!"

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው በአካለ ሥጋ መሆኑን የሚያስተምሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በጥሙና እንመልከት፡—

### 1. ትንሣኤ የሚለው ቃል ቀኣሳዊ የሆነ አካልን ብቻ የሚያመለክት ነው

የሐዲስ ኪዳንን የትንሣኤ ትምህርት በጠለለ መልኩ ለመረዳት አይሁዶች ስለ ሙታን ትንሣኤ ያላቸውን ትምህርት በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ከሉቃስ በስተቀር ሁሉም የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍያን አይሁዶች ስለሆኑ (ቈላስይስ 4÷11:14) እንዲሁም ሐዲስ ኪዳን

[8] የመጨረሻውን ንጽጽር ቃል በቃል ከተረጐምነው "ነፍሳዊ አካል" "መንፈሳዊ አካል" ብለን ነው። በዚሁ መጽሐፍ ሐዋርያው፣ "መንፈሳዊ ሰው" (1ቆሮንቶስ 2÷15) የሚለውን ቃል የተጠቀመው ቀኣሳዊ አካል የሌለው፣ የማይታይና የማይጨበጥ ሰውን ለማመልከት ሳይሆን ቀኣስ አካላዊ የሆነ፣ ደምና ሥጋ ያለውን ነገር ግን ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ ቍጥጥር ሥር ያለውን ሰው ለማመልከት ነው (1ቆሮንቶስ 3÷1፤ 14÷37፤ ገላትያ 6÷1)። በተጨማሪ "መንፈሳዊ ምግብ" "መንፈሳዊ መጠጥ" የሚለው ቃል፣ የብሉይ ኪዳኑን መናና ከዐለት የፈለቀው ውሃ ነው። ውሃውና ምግቡ መንፈሳዊ የተባሉበት ምክንያት ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለሆኑ እንጂ መንፈስ ስለሆነ አይደለም። በዚሁ ዐውደ ምንባብ ሐዋርያው ቅድመ ትንሣኤ አካል የማይበሰብስ ሆኖ እንደሚነሣ እንጂ፣ ረቂቅ መንፈስ እንደሚሆን አያስተምርም (1ቆሮንቶስ 15÷51-52)። ስለዚህ ክፍሉን ከዐውዳዊ ትርጕሙ ገንጥለን/አላቀን ልንተረጕመው አይገባም።

*ስለ ትንሣኤ ሙታን የሚያስተምረው ትምህርት፣ ከብሉያት አስተምህሮ ጋር ተያያዥነት ያለው ስለሆነ።*

“*ለዘብተኛ አቋም*” *አላቸው በመባል የሚታወቁት ሰዱቃውያን በሙታን ትንሣኤ አያምኑም ነበር (ማቴዎስ* 22÷23)። *በአንጻሩ ደግሞ ፈሪሳውያን በሙታን ትንሣኤ ያምናሉ (ሐዋርያት ሥራ* 23÷8)። *ሰዱቃውያን ትንሣኤ ሙታን ላለመኖሩ እንደ ምክንያት ያቀረቡት ጒዳይ ስለማግባትና ስለመጋባት ነበር፤ ይህም ትንሣኤ ሙታን የአካል እንደ ሆነ ታሳቢ ያደረገ ንግግር መሆኑ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስም የመለሰው መልስ ትንሣኤ ሙታን የአካል እንደ ሆነ ነገር ግን ከትንሣኤ በኋላ ማግባትና መጋባት እንደማይኖር የሚያስረዳ ነው (ማቴዎስ* 22÷28)። *ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ቀድሞ ፈሪሳዊ በነበሩ ሰዎች ነው። አይሁዶች በተለይ ደግሞ ፈሪሳውያን ሰው የተፈጠረው ከምድር ዐፈር እንደ ሆነ (ዘፍጥረት* 2÷7)፣ *ወደ ዐፈርም እንደሚመለስ (መክብብ* 12÷7)፣ *በትንሣኤም ቀን ወደ ዐፈርነት ከተለወጠው አካሉ በእግዚአብሔር ኪነ ጥበብ ሕያው ሆኖ ከሙታን እንደሚነሣ (ዘዳግም* 32÷39፤ 1*ሳሙኤል* 2÷6፤ *ኢዮብ* 19÷25-27፤ *መዝሙር* 49÷14-15) *ያምናሉ።*

*የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አስተምህሮ ንጉሥ ዳዊት የእግዚአብሔር ቅዱስ የሆነው ኢየሱስ መበስበስን እንግማያይ ተንብዮ ነበር (መዝሙር* 16÷10)። *ጴጥሮስ የንጉሥ ዳዊትን ትንቢት በተመለከተ እንዲህ በሏል፣* "*ይህንን አስቀድሞ በማየቱ እርሱ በሲኦል እንደማይቀርና ሥጋውም እንግማይበሰብስ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ተናገረ*" *(ሐዋርያት ሥራ* 2÷31)። *በዚህ ቦታ* “*ሥጋ*” *ተብሎ የተተረጐመው የግሪክ ቃል* ("*ሳርክ*" σὰρξ) *ሊበሰብስ እንደሚችል ነገር ግን በእግዚአብሔር ከሃሌ ኵሉነት በመስበስን ሳያይ እንደማይበሰብስ ሆነ ከሙታን እንደ ተነሣ ያስተምራል። ሐዋርያው ጳውሎስም ይህን የዳዊት ትንቢት በመጥቀስ ኢየሱስ፣* “*እንዳልበሰበሰና እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው ለማረጋገጥ...*'*ቅዱስህ መበስበስን እንዲያይ አትፈቅድም*' *ይላል*” *(ሐዋርያት ሥራ* 13÷34:35)።

*ኢየሱስ ሰዱቃውያን በሙታን ትንሣኤ ባለማመናቸው፣* “'*ቅዱሳት መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል ስለማታውቁ ትስታላችሁ*” *(ማቴዎስ* 23÷29) *ሲል ተናግሯቸዋል። እንዲሁም ዘፀአት* 3÷6:15 *በመጥቀስ፣* “'*እኔ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቀብ አምላክ ነኝ*'። *እግዚአብሔር የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም*” *(ማቴዎስ* 23÷32) *ሲል አስተምሯል።*

*ነቢዩ ኢሳይያስ፣* “*ነገር ግን ሙታን ሕያዋን ይሆናሉ፤ በድናቸውም ይነሣል። እናንት በዐፈር ውስጥ የምትኖሩ፣ ተነሡ፤ በደስታም ዘምሩ። ጠልህ እንደ ንጋት ጠል ነው፤ ምድር ሙታንን ትወልዳለች*” *(ኢሳይያስ* 26÷19) *የሚለው ትምህርቱ የሞተው አካል እንደሚነሣ ይህም የሙታን ትንሣኤ የአካል እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው።*

*ዳንኤል፣* “*በምድር ዐፈር ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ አንዳንዶቹ ለዘላለም ሕይወት፣ ሌሎቹም ለውርደትና ለዘላለም ጒስቍልና ይነሣሉ*” *(ዳንኤል* 12÷2) *የሚለው ትንቢቱ ትንሣኤ ሙታን የአካል እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። በተመሳሳይ መልኩ ኢየሱስ ትንሣኤ ሙታን ከሚያገኙ ሰዎች ግማሹ ወደ ዘላለም ሕይወት ግማሾቹ ደግሞ ወደ ዘላለም ሞት እንደሚሄዱ አስተምሮአል (ዮሐንስ* 5÷28)።

*ማርያምና ማርታ ወንድማቸው አልዓዛር በትንሣኤ ቀን እንደሚነሣ ተስፋ እንደሚያደርጉ በተጨማሪ ኢየሱስ በትንሣኤ ቀን ብቻ ሳይሆን ዛሬም ሙታንን የማስነሣት ኀይል ከገለጸ በኋላ*

አልዓዛርን ከሙታን ማስነሣቱ ትንሣኤ ሙታን የአካል እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምር ነው (ዮሐንስ 11÷38-44)።

ከእነዚህም ሆኑ ከእነዚህ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው የብሉይና የሐዲስ ኪዳን ምንባባት በግልጽ የምንረዳው እውነት፣ ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት ስለ ትንሣኤ የሚያስተምሩት ትምህርት ተደጋጋፊ እንዲሁም እርስ በእርሱ የሚጣጣም መሆኑን ነው። ይኸውም መጽሐፍ ቅዱስ ትንሣኤ የሚለውን ቃል የሚጠቀመው ቊሳዊ አካል ከሙታን መነሣቱን ለማመልከት ብቻ ነው። ዕብራውያን በተለይ ፈሪሳውያን የጻድቃን የወደፊት ሁኔታ አስመልክቶ የተለያየ አመለካከት ቢኖራቸውም፣ ሁሉም ግን ትንሣኤን ቊሳዊ አካል በጊዜዪዊነትም ሆነ በቋሚነት ከመነሣት ጋር ብቻ ነበር የሚያያይዙት።

ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈሪሳውያን ግብዝነት ደስተኛ ባይሆንም፣ ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤ ባለመቀበላቸው ቢነቅፋቸውም፣ ትንሣኤ በሚለው የቃል ፍቺ ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው (ማቴዎስ 22÷23-32)። ጳውሎስ ቀድሞውኑ ፈሪሳዊ ስለነበር ሥቃይ የደረሰብኝ በሙታን ትንሣኤ በማመኔ ነው ብሉ ነበር (ሐዋርያት ሥራ 23÷6-8)።

በአጠቃላይ ትንሣኤ የሚለው ቃል ያለው ትርጒም የሞተ ሰው አካል በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት ሕይወት ማግኘት ማለት ነው።

## 2. የሐዋርያው ጳውሎስ አስተምህሮ

ሐዋርያው ጳውሎስ እጅግ ጥንታዊ ነው የሚባለውን የቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫ ጠቅሶ በጻፈበት ክፍል ላይ፣ የክርስቶስን ሞት ከገለጸ በኋላ የሃይማኖት መግለጫው እንዲህ ያላል፣ "ቅዱሳት መጻሕፈት እንደሚሉት ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረ፤ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ተነሣ" (1ቆሮንቶስ 15÷3-4)። ከዚህ ክፍል በግልጽ የምንግረው እውነት፣ ሞቶ የተቀበረው አካል ከሙታን እንደ ተነሣ ነው። ይህም የሞተው፣ የተቀበረውና ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው አካል አንድ መሆኑን አመላካች ነው። በዚሁ ምዕራፍ ሐዋርያው የስንዴ ቅንጣትን በምሳሌነት በመጠቀም አራት ጊዜ የተዘራው የስንዴ ቅንጣት እንደ በቀለ ይገልጻል፣ "…ይዘራል…ይነሣል…ይዘራል…ይነሣል…ይዘራል…ይነሣል ይዘራል…ይነሣል…" (1ቆሮንቶስ 15÷42-44)። ልክ እንደዚሁ ሁሉ ሞቶ የተቀበረው የክርስቶስ አካል በትንሣኤ እንደ ተነሣ የሚያስተምር ነው።

ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ሲመጣ፣ "ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል" (ፊልጵስዩስ 3÷21) የሚለው የሐዋርያው አነጋገር የተዋረደው የእኛ ሥጋ ልክ እንደ እርሱ ሥጋ እንደሚለወጥ ሲገልጽ፣ እርሱ ራሱ "በተለወጠ ሥጋ" እንዳለ የሚያስተምር ነው። በዚህ ክፍል የቅዱሳኑንም ሆነ የክርስቶስን አካል ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለውና የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች "ሥጋ" ብለው የተረጐሙት "ሶማ" (σῶμα)[9] የሚለው የሐዲስ ኪዳን ግሪክ፣ ዘወትር የሚጨበጠውን የሚዳሰሰውን አካል የሚያመለክት ነው። የክርስቶስ ትንሣኤ

[9] "ሶማ" (σῶμα) በሚለው የግሪክ ቃል ላይ ሰፊ ጥናት ያካሄዱት የነገረ መለኮት ምሁሩ ሮበርት ጋንድሪ ቃሉ በተለይ ደግሞ በጳውሎስ ጽሑፎች ውስጥ ሁል ጊዜ የሚጨበጠውን፣ የሚታየውን ቊሳዊ አካል እንደሚያሳይ አስረድተዋል። የክርስቶስን ቅድመ ትንሣኤ እንዲሁም ድኅረ ትንሣኤ አካል ለማሳየት "ሶማ" የሚለው የግሪክ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል (ለምሳሌ ዮሐንስ 2÷21፤ 1ቆሮንቶስ 15÷44፤ ፊልጵስዩስ 3÷21 ያነጻጽሯል)። Robert Gundry, *Soma in Biblical Theology with Emphasis on Pauline Anthropology* (London: Cambridge University Press, 1976), 126, 124.

በመንፈስ ቢሆን ኖሮ፣ ሐዋርያው "ሥጋ" ከሚለው ቃል ይልቅ መንፈስ የሚለውን ቃል ይጠቀም ነበር። የጻቃን ዕጣ ፈንታቸው በትንሣኤ ሥጋ ከሙታን መነሣት ከሆነ፣ ክርስቶስም ከሙታን የተነሣው በትንሣኤ ሥጋ ነው ማለት ነው። ጻድቃን ከመሞት ወደ አለመሞት የመለወጣቸው ሂደት ቀሳዊ እንደ ሆነው ሁሉ፣ የክርስቶስም ትንሣኤ በቀሳዊ አካል እንደ ሆነ በንጽጽር የሚያሳይ ነው።

ሐዋርያው፣ "ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው የእርሱ መንፈስ በእናንተ የሚኖር ከሆነ፣ ክርስቶስን ከሙታን ያስነሣው፣ በውስጣችሁ በሚኖረው በመንፈሱ *ሟች ለሆነው ሰውነታችሁ ሕይወትን ይሰጣል*" (ሮሜ 8÷11) በዚህ ክፍል ሐዋርያው በክርስቶስ አካል ላይ መታደስ እንደ ተካሄደ እንጂ፣ አካሉ በመቃብር እንዳልቀረ ታሳቢ ያደረገ ንግግር ነው[10]።

ሐዋርያው ጳውሎስ በቈላስይስ 2÷9፣ "የመለኮት ሙላት ሁሉ በአካል በእርሱ ይኖራልና" ሲል "ይኖራል" ("ካቶይኬ" "κατοικεῖ") የሚለውን ቃል የተጠቀመው የአሁን ጊዜ ግሥ ነው፤ ይህም አምላክ የመሆን ባሕርዩ ("የመለኮት ሙላት" "ቴዎቴቶስ" "θεότητος")[11] በሰውነቱ/በሥጋው ("ሶማቲኮስ" "σωματικῶς") የሚኖረው፣ ሐዋርያው ይህን መልእክት እስከሚጽፍበት ጊዜ ድረስ ኢየሱስ አካል/ሥጋ እንዳለው የሚያሳይ ነው።

ሉቃስ፣ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ላይ ባቀረበው ዘገባ ጳውሎስ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እንደ ንጉሥ ዳዊት ሥጋ በመቃብር ውስጥ እንዳልበሰበሰ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የሞትን ጣር አጥፍቶ እንዳስነሣው ገልጾአል (ሐዋርያት ሥራ 13÷34-37)። በተጨማሪም ይህ የክርስቶስ ኢየሱስ የአካል ትንሣኤ የትንቢት ፍጻሜ እንደ ሆነ ተገልጾአል (መዝሙር 16÷10)። የክርስቶስ አካል ከንጉሥ ዳዊት አካል ጋር ተነጻጽሮ መቅረቡ እንዲሁም የንጉሥ ዳዊት መቃብር ዛሬም ድረስ እንዳለና የኢየሱስ መቃብር ግን ባዶ መሆኑ፣ የአካል ትንሣኤን አያመለክትም ብሎ ማሰብ እጅግ ሲበዛ አስቸጋሪ ነው።

በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ዐሥራ አምስት በዝርዝር የቀረበው መረጃ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአካል መሆኑን በግልጽ የሚያስተምር ነው። ዋና ዋና የሚባሉትን ነጥቦች እንመልከት[12]:—

---

[10] "መለከት ይነፋል፤ ሙታን የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን" (1ቆሮንቶስ 15÷52) በሚለው ክፍል፣ የሚበሰብሰብሰው አካል "እንደማይበሰብስ" ሆኖ "እንደሚለወጥ" የሚገልጸው ገለጻ ያው የሚበሰብሰው አካል እንደማይበሰብስ ሆኖ እንደሚለወጥ የሚገልጽ ነው። "እኛም እንለወጣለን" የሚለው የግሪክ ቃል ("አልላጌሶሜታ" "ἀλλαγησόμεθα") መጥፋትን ሳይሆን መታደስን/መሻሻልን የሚያሳይ ነው። ይህም የሚሞተውና የማይሞተው የተባለው አካል አንድ እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው፤ በተለይ ቁጥር 53 ይህን ጉዳይ ግልጽ ያደርገዋል፣ "የሚጠፋው የማይጠፋውን፣ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና"። "መልበስ" የሚለው የግሪክ ቃል ("ኢንዲሳስታይ" "ἐνδύσασθαι") ልብስን ከመልበስ ጋር አንድ ዐይነት ሲሆን፣ (ማርቆስ 6÷9፤ ኤፌሶን 4÷24)፣ ይህም "ይበሰብሳል" የተባለው ቅድመ ትንሣኤ አካል፣ ለውጥ እንደሚካሄድለት እንጂ እንዳማይጠፋ ግልጽ የሚያደርግ ነው።

[11] "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀው መናፍቃው ድርጅት መምህራን ይህ ክፍል በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ አብ መኖሩን ያመለክታል፣ ስለዚህም ኢየሱስ አብ ነው ለማለት በአስረጅነት ሊጠቀሙበት ይሞክራሉ። ክፍሉ "በኢየሱስ ውስጥ አብ በሙላት ይኖራል" ሳይሆን፣ በኢየሱስ ውስጥ "የአምላክነት ባሕርይ በሙላት" ("ቴዎቴቶስ" "θεότητος") አለ ነው የሚለው። ይህም የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት አመልካች እንጂ አብ መሆኑን የሚያስተምር አይደለም።

[12] ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ፤ *የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* (ራእይ አሳታሚ ድርጅት፤ 1991 ዓ.ም), 100-103 ላይ ነው።

### ሀ. "ከእናንተ አንዳንዶቹ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ?" (ቊጥር 12)

*ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈው ከአቴና ትንሽ ኪሎ ሜትር ወረድ ብላ በምትገኘው ቆሮንቶስ ነው። በዚያ የሞቱ ሰዎች ዳግም ሕይወት ያገኛሉ የሚለው ትምህርት ተረት ነበር (ሐዋርያት ሥራ 17፥32)። አንድ ግሪካዊ ወደ ፊት ሕይወት በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ይቀጥላል የሚለው ትምህርት የሚቀበለው እንጂ የሚሰናከልበት ጉዳይ አይደለም፤ ግሪካውያንን የሚያሰናክላቸው የአካል ትንሣኤ ወይም በዚሁ አካል ዳግም ሕይወት ያገኛል የሚለው ትምህርት ነው*[13]::

### ለ. "የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም" (ቊጥር 37)

*የዘር ፍሬ ከሚበቅለው ፍሬ እንደሚለይ የትንሣኤም አካል ከሚሞተው አካል የተለየ ነው። ነገር ግን በተዘራው ማለትም በሞተው ዘርና በበቀለው ዘር መካከል በክፍለ ህዋስ ወይም በመሠረታዊ ተፈጥሮአቸውም ሆነ በታሪካቸው ልዩነት እንደሌላቸው ሁሉ የትንሣኤ አካል ከሞተው አካል ያለው አንድነት እንደዚሁ ነው።*

### ሐ. "የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፤ በኀይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ" (ቊጥር 42-44)

*በክፍሉ አራት ጎድ ነገሮች አብረው ተነጻጽረዋል። በመበስበስ፣ ባለመበስበስ፤ በውርደት፣ በክብር፤ በድካም፣ በኀይል፤ ፍጥረታዊ፣ መንፈሳዊ። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥንዶች ስለሚሞተው አካል የተሰጡት አሉታዊ ገለጻዎች ናቸው። መበስበስ፣ ውርደት፣ ድካም ከመጀመሪያው አካም የተገኙ አሉታዊ ውርሶች ናቸው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጎዶች ውስ ስለ ትንሣኤ አካል የቀረቡት ገለጻዎች የሚጠቁሙት አሉታዊ የሆኑት የውድቀት ውጤቶች እንደሚለወጡ ነው። በክፍሉ ላይ የቀረቡት የጳውሎስ ማስረጃዎች የሐሳብ ፍሰታቸው ወጥነት ያለው ነው። አራተኛው ጥንድ እንደ ላይኞቹ ሦስቱ አብረው በንጽጽር የቀረበ ነው። ይኸውም ለውድቀት መንሥኤ ስለሆነው አካልና ከውድቀት ለመነሣት ምክንያት ስለሆነው አካል ነው። "ፍጥረታዊ አካል" የተባለው የኀጢአት አሉታዊ ውጤት የሆነው ነው። በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከምድር ዐፈር እንዳበጀው፣ ይህንንም አካል፣ "መልካም ነው" እንዳለ እንመለከታለን (ዘፍጥረት 1፥26-31)።*

*አንደኛ ቆሮንቶስ 2፥14-15 ስለ መንፈሳዊ ሰው ይናገራል። "መንፈሳዊ ሰው" ማለት ግን ቊሳዊ አካል የሌለው መንፈስ ብቻ የሆነ ማለት አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ቊጥጥር ሥር ያለ ማለት ነው። በአጠቃላይ "ፍጥረታዊ አካል" በእግዚአብሔር ቢፈጠርም፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ "መልካም ነው" ቢለውም እንኳ፣ በኀጢአት አማካይነት ግን ይህ አካል ተበላሽቶአል።*

---

[13] ዝኒ ከማሁ ከF.F Bruce, *The Acts of the Apostles. The Greek Text with Introduction and commentary* 2nd edition (Grand Rapids: Eerdmans, 1952), 340 (on Acts 17:32) ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

**መ. "እንዲሁ ደግሞ፣ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ" (ቁጥር 45)**

በዚህ ክፍል ላይ የተነጻጸሩት ነፍስ (ግሪክ "ሱቼ" "ψυχὴν") እና መንፈስ (ግሪክ "ኒውማ" "πνεῦμα") መፈታት ያለባቸው ከቁጥር 44 አንጻር ነው:: ስለዚህ በቁጥር 44 ላይ ያለው ንጽጽር በሚሞተው አካል (ለኀጢአትና ለውጤቱ ሰለባ የሆነው) እንዲሁም በትንሣኤ አካል (ከኀጢአት ተጽእኖ ውጪ የሆነው) መካከል ነው:: በቁጥር 45 ላይም የምናገኘው ንጽጽር ይኸው ነው:: አካም በሚፈጠርበት ጊዜ ኀጢአተኛ ስላልነበር የኀጢአትም ጥቃት አልደረሰበትም:: ነገር ግን በኀጢአት በመውደቁ ምክንያት ተበላሸ፣ ረከሰ፣ ደከመ፣ ሞተ::

**ሠ. "የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው" (ቁጥር 47)**

ይህ ክፍል ኢየሱስን ሰው ይለዋል:: ለኀጢአት ክፍያ ኢየሱስ ሰብአዊነቱን ትቶአል ከሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት በቀጥታ ይጣረሳል:: የትንሣኤ አካል ዐፈር ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ለሕይወት ብቁ እንዲሆን የተለወጠ ነው (ቁጥር 48)::

**ረ. "ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፤ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም" (ቁጥር 50)**

የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር ብቻ መጥቀስ ይወዳሉ:: ነገር ግን ተከታዩ ዐረፍተ ነገር የክፍሉን ሐሳብ በተሟላ መልኩ ይገልጻል:: የሚሞተው አካላችን ችግሩ ቁሳዊ አካል መሆኑ ሳይሆን፣ ስለተበላሸ፣ የሚበሰብስ ስለሆነ ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሥጋና ደም" የሚለውን አገላለጽ በምድር ብቻ የተወሰነ መሆንን፣ ድካምን የሚገልጽ ሥዕላዊ ቋንቋ ነው (ማቴዎስ 16÷17፤ ገላትያ 1÷16፤ ኤፌሶን 6÷12፤ ዕብራውያን 2÷14)::

የእግዚአብሔርን መንግሥት ያለመውረሳችን ምክንያቱ በኀጢአት መውደቃችን ነው (1ቆሮንቶስ 6÷9-10፤ ገላትያ 5÷12):: ስለዚህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ቁሳዊ አካልን መተው ሳይሆን (1ቆሮንቶስ 15÷50) የተበላሸውን ሁኔታችንን የሚያድስና የሚያስተካክል የመንፈስ ቅዱስ ሰማያዊ ሕይወት ማግኘት ነው (1ጴጥሮስ 1÷4)::

**ሰ. "ሙታን የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ፤ እኛም እንለወጣለን:: ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋል" (ቁጥር 52-53)**

ጳውሎስ በዚህ ክፍል እያጠናከረ ያለው ትምህርት፣ ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ መለወጥ የግድ እንደሚያስፈልገው ነው:: እሱን በማጥፋት መንፈሳዊ በሆነው አካል መቀየር አስፈላጊ አይደለም:: ይህ የተበላሸ፣ ሟች የሆነው ሰብአዊነት የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን መልበስ ያስፈልገዋል:: አሁን ያለን ይህ አካላችን ቀጣይነት ይኖረዋል፤ ነገር ግን የሚበሰብሰው ክፍል ሊለወጥ ይገባዋል::

**ሸ. “በዚያን ጊዜ ሞት ድል በመንሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል” (ቀኍጥር 54)**

ትንሣኤ ሞትን ድል የሚያደርገው የሚሞተው አካል በሕይወት ሲታደስ ብቻ ነው።

## 3. ሐዋርያው ጴጥሮስ ትንሣኤ ሙታን የአካል መሆኑን ሰብኳል

እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉ ሐዋርያው ጴጥሮስም የኢየሱስ አካል እንደ ንጉሥ ዳዊት በመቃብር ቀርቶ እንዳልበሰበሰ ነገር ግን በእግዚአብሔር ኪነ ጥበብ ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሣ ሰብኳል (ሐዋርያት ሥራ 2÷25-32)። እንዲያውም ሐዋርያው ጴጥሮስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደ በላና እንደ ጠጣ ገልጸአል። ሉቃስና ዮሐንስም ጌታ ከትንሣኤው በኋላ መብላቱንና መጠጣቱን ገልጸዋል (ዮሐንስ 21፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷39-40)።

## 4. ወንጌላት ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን እንደ ተነሣ ያስተምራሉ

የማቴዎስ ወንጌል የክርስቶስ ትንሣኤ ቍሳዊ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራል። ወደ መቃብሩ ስፍራ የሄዱት ሴቶች፣ “ወደ ኢየሱስ ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት” (ማቴዎስ 28÷9)። እግሩን “ይዘው” የሚለው ቃል (“ኤክራቴሳን” “ἐκράτησαν”) የክርስቶስ የትንሣኤ አካል የሚጨመጥ የሚዳሰስ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ይህም ትንሣኤው ቍስአዊ መሆኑን ያሳያል። የአይሁድ መሪዎች የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት አስክሬኑን ወስደዋል ብለው እንዲያወሩ ለወታደሮች ትእዛዝ መስጠታቸው (ቀኍጥር 13) መቃብሩ ባዶ መሆኑን ይህም ትንሣኤው የአካል መሆኑን በግምት ውስጥ ያስገባ አነጋገር ነው።

የማርቆስ ወንጌል የክርስቶስ ትንሣኤ የአካል መሆኑን በግልጽ ያስተምራል። ማርቆስ መቃብሩ ባዶ መሆኑን መግለጹ ትንሣኤው የአካል መሆኑን የሚያስተምር ነው “አትደንግጡ፤ የምትፈልጉት የተሰቀለውን የናዝሬቱ ኢየሱስን ነው፤ እርሱ ተነሥቶአል፤ እዚህ የለም፤ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ ይኸውላችሁ” (ማርቆስ 16÷6)። “እርሱን ያኖሩበት ስፍራ ይኸውላችሁ” (“ἴδε ὁ τόπος ὅπου ἔθηκαν αὐτόν”) የሚለው ማረጋገጫ የኢየሱስ ክርስቶስ አካል በኖረበት ስፍራ እንደሌለ፤ ከሙታን መነሣቱ ቍሳዊ መሆኑን ያሚያስተምር ነው። አር. ቲ. ፍራንስ የተባሉት የነገረ መለኮት ትምህርተ ዘለቅ፣ “ተነሥቶአል” ግሪክ “ኤግሬቴ” (ἠγέρθη) የሚለው ቃል በተገብሮ ግሥ (passive) መቀመጡ፣ የሞተው አካል ራሱ ከሙታን መነሣቱን አመላካች እንደ ሆነ ያስረዳሉ[14]።

የሉቃስ ወንጌል የክርስቶስ ትንሣኤ የአካል መሆኑን በግልጽ ያስተምራል። “ሴቶቹም ከመፍራታቸው የተነሣ ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፣ ሰዎቹ እንዲህ አሏቸው፤ ሕያው የሆነውን እርሱን ለምን ከሙታን መካከል ትፈልጋላችሁ? እርሱ ተነሥቶአል! እዚህ የለም” (ሉቃስ 24÷5-6)። ሴቶቹ ፈልገው የመጡት የኢየሱስን አስክሬን ነው። መልእክተኞቹ ግን “ሕያው የሆነውን እርሱን ለምን ከሙታን መካከል” የሚለው ንግግራቸው ጌታ ተቀብሮበት በነበረው መካነ መቃብር ብዙዎች ሞተው የቀሩበት በአንጻሩ ኢየሱስ ሕያው ሆኖ ከሙታን ስለተነሣ “በዚህ የለም” መባሉ ኢየሱስን ከሙታኑ ጋር የሚያነጻጽር ብቻ ሳይሆን መቃብሩም ባዶ መሆኑን የሚያስተምር ነው። ይህም ትንሣኤው የአካል መሆኑን ያስተምራል።

---

[14] R. T. France, *The Gospel of Mark: The New International Greek Testament Commentary,* Eds. Howard Marshall, Donald A. Hagner, (Grand Rapids: Eerdmans, 2002), 680.

ሉቃስ የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል ሥጋና ደም ያለው አካል መሆኑን እንዲሁም መዳሰሱን፣ መነካቱን፣ መብላተ መቻሉን ዘግቦልናል (ሉቃስ 24÷36-43)፡፡

የዮሐንስ ወንጌል የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የአካል መሆኑን በግልጽ ያስተምራል፡፡ ዮሐንስ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን እንደሚነሣ እርሱ ራሱ የተነበየውን ትንቢት ዘግቦልናል፣ "አይሁድም፣ 'ይህን ሁሉ ለማድረግ ሥልጣን እንዳለህ የሚያረጋግጥ ምን ተአምራዊ ምልክት ታሳየናለህ?' አሉት፡፡ ኢየሱስም 'ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፤ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ' ብሎ መለሰላቸው፡፡ አይሁድም፣ 'ይህን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አርባ ስድስት ዓመት ፈጅቶአል፤ ታዲያ አንተ እንደት በሦስት ቀን መልሰህ ታነሣዋለህ?' አሉት፡፡ ቤተ መቅደስ ሲል ግን፣ ስለ ገዛ ሰውነቱ መናገሩ ነበር፡፡ ከሙታን ከተነሣ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርቱ ምን እንደ ተናገረ አስታወሱ፤ መጻሕፍትንና ኢየሱስ ያለውንም ቃል አመኑ"፡፡ (ዮሐንስ 2÷18-22)፡፡ ይህ ክፍል ኢየሱስ "አፍርሱት" ያለውንና የፈረሰውን ሥጋ/አካል (ግሪክ "ሶማ" "σῶμα") በሦስተኛው ቀን ማስነሣቱ፣ ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምር ነው፡፡

መግደላዊት ማርያም፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ ባዶ መቃብር ማየታቸውን ዮሐንስ ዘግቦልናል (ዮሐንስ 20÷1-15)፡፡ ይህም ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቶማስን "ጣትህን ወደዚህ አምጣ፤ እጆቼንም ተመልከት፤ እጅህን ዘርጋና በጐኔ አስገባ፤ አትጠራጠር፤ እመን አለው" (ዮሐንስ 20÷27) የሚለው አነጋገር የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል እንደሚጨበጥ እንዲሁም በስቅላቱ ቀን በጐኑና በእጁ የነበሩት ጠባሶች/እትራት ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምር ነው፡፡ ዮሐንስ፣ ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደ ተነጋገረ፣ ምግብ እንደበላ፣ በባሕር ዳር አጠገብ እንደ ተጓዘ ወዘተ የዘገበልን ዘገባ ኢየሱስ በአካል ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሣ የሚያሳይ ነው[15]፡፡

## ፭. የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ባዶ ነው

ኢየሱስ ክርስቶስ ተቀብሮበት የነበረው መቃብር ከእሑድ በኋላ ባዶ መገኘቱ ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ በግልጽ የሚያስተምር ነው፡፡ መላእክት፣ "እርሱ በዚህ የለም፤ እንደ ተናገረው ተነሥቶአል፤ ኑና ተኝቶበት የነበረውን ቦታ እዩ" (ማቴዎስ 28÷6) ማለታቸው እንዲሁም ጴጥሮስ ወደ መቃብሩ ከገባ በኋላ፣"ከተልባ እግር የተሠራውን ከፈን አየ፤ እንዲሁም በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ አየ፤ ይህም ጨርቅ ከከፈኑ ተለይቶ እንደ ተጠቀለለ" (ዮሐንስ 20÷6-7) ማየቱ ትንሣኤው የአካል መሆኑን አስተማሪ ነው (ሐዋርያት ሥራ 13÷29-30)፡፡

ዮሐንስ፣ ኢየሱስን ከትንሣኤው በኋላ ከማየቱ በፊት ባዶ መቃብሩን በማየቱ ብቻ ጌታ መነሣቱን ማመኑ (ዮሐንስ 20÷8) ትንሣኤው የአካል መሆኑን አመላካች ነው[16]፡፡

---

[15] ዮሐንስ፣ በሌላ ስፍራ ኢየሱስ ክርስቶስን ሰምተነዋል፣ አይተነዋል፣ ዳሰነዋል፣ ተመልክተነዋል ወዘተ የሚለው ገለጻው (1ዮሐንስ 1÷1-3) የኢየሱስ ክርስቶስን ቅድመ ትንሣኤ ሕይወት ብቻ ሳይሆን፣ ድኅረ ትንሣኤ ሕይወትንም ሊያመለክት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡

[16] Norman L. Geisler, *The Battle for the Resurrection* (Nashville: Thomas Nelson, 1990), 42.-43.

## 6. የኢየሱስ የትንሣኤ አካል ተጨብጦአል

ቶማስ፣ መግደላዊት ማርያም፣ ደቀ መዛሙርቱ ወዘተ ኢየሱስን ከትንሣኤው በኋላ እንደ እንደ ጨበጡት/እንደ ዳሰሱት በግልጽ በሚያስተምርበት ሁኔታ (ዮሐንስ 20÷27:28:17፤ ማቴዎስ 28÷9፤ ሉቃስ 24÷39) ትንሣኤው የአካል ትንሣኤ አይደለም ማለት ስሕተት ነው[17]::

## 7. የኢየሱስ የትንሣኤ አካል ሥጋና ዐጥንት አለው

ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ መንፈስ እንዳልሆነ ያረጋገጠላቸው እንዲዳስሱት በመፍቀድ ብቻ ሳይሆን፣ እርሱ ሥጋና ዐጥንት እንዳለው ነገር ግን መንፈስ ሥጋና ዐጥንት እንደሌለው በመግለጽ ነው፣ "እጆቼንና እግሮቼን ተመልከቱ፤ እኔው ራሴ ነኝ። ደግሞም ንኩኝና እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና" (ሉቃስ 24÷39)።

በርግጥ የሚበሰብስ፣ "ሥጋና ዐጥንት የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም" (1ቆሮንቶስ 15÷50) ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል የሚበሰብስ ስላልሆነ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ ይችላል፤ ምክንያቱም በመበስበስ የተዘራው አካል እንደማይበሰብስ ሆኖ ይነሣልና (1ቆሮንቶስ 15÷42)[18]።

## 8. ኢየሱስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው

በአብ ቀኝ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ልጅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው (ሐዋርያት ሥራ 17÷31፤ 1ቆሮንቶስ 15÷47፤ 1ጢሞቴዎስ 2÷5)።

በሐዋርያት ሥራ 17 ጳውሎስ ስለ ሙታን ትንሣኤ እያስተማረ ቊጥር 32 ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ ሰው ሆኖ እንዳለ ይያገር ነበር ቊጥር 31። በአንደኛ ቆሮንቶስ 15÷47 ጳውሎስ ስለ ሁለት ሰዎች እየተናገረ ነው ያለው። የአንደኛው ሕይወት ሰማያዊ ነው፤ የሌላ ደግሞ ምድራዊ ነው። ይህ የሚያመለክተን አሁን እንኳ ኢየሱስ ሰው ሆኖ እንደለ ነው እንጂ በአንድ ወቅት ሰው የነበረና አሁን ሰውነቱን ሰው መሆኑን የተወ ማለት አይደለም። አንደኛ ጢሞቴዎስ 2÷5 በዚህ ክፍል ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜ እንኳ ሰው ባየሆን ኖሮ ሰው ማለት ባላስፈለገው ነበር። ኢየሱስ አማላጅ እንጂሆን ያደረገው የእኛን ደምና ሥጋ መውሰዱ ነበር። ኢየሱስ የእኛን ደምና ሥጋ ቀይሮ መንፈስ ሆኖ ካለ አማላጅነቱ እውን ሊሆን አይችልም።

## 9. ኢየሱስ ራሱ እኔ መንፈስ አይደለሁም ብሎአል

በሉቃስ 24÷39 ኢየሱስ መንፈስ እንዳልሆነ ለማስረገጥ የእጁንና የእግሩን ችንካር በማሳየት እኔ ራሴ ነኝ ብሎአል። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ኢየሱስ ሥጋና ደም አላኝ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱን ዳሱኝ ያለው የደቀ መዛሙርቱን እምነት ለማገዝ በመነሣቱ እንዲያምኑ ነበር የሚለው ትንታኔ ፍጹም ከእውነት የወጣ ነው። እንዴት ደቀ መዛሙርቱን እያታለለ እምነታቸውን ያጠናክራል?

---

[17] ዝኒ ከማሁ፤ 43።

[18] ዝኒ ከማሁ።

## 10. ወንጌላት የኢየሱስ አካል ሕያው እንደ ሆነ ይናገራሉ

መላእክት የኢየሱስ አካል በመቃብሩ ስፍራ ያለመገኘቱን ማብሠራቸው ኢየሱስ በአካል መነሣቱን ያሳያል (ማቴዎስ 28÷6፤ ማርቆስ 16÷6)። የኢየሱስ ክርስቶስ የትሣኤ አካል በስቅላቱ ጊዜ በእጆቹ፣ በእግሮቹና በጐኑ የነበሩት ቊስሎች ወይም እትራት ነበሩበት (ሉቃስ 24÷39-40፤ ዮሐንስ 20÷20:25-27)። ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ በልቶአል (ሉቃስ 24÷41-43፤ ሐዋርያት ሥራ 14፤ ዮሐንስ 21÷12-15)።

## 11. ኢየሱስ ሰብአዊ ሕይወቱን በትንሣኤ መልሶአል

ኢየሱስ አካላዊ ሕይወቱን የሰጠው ያኖረው ለዘላለም ሊተወው ሳይሆን በክበረ ሁኔታ ደግም ሊያስነሣው ነው ዮሐንስ 10÷17-18። "ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና" ቊጥር 17 የሚለው ገለጻ የሚያመለክተን ነፍሱን የሚያኖርበት ምክንያት ለማስነሣት ነው (በዚህ ክፍል ሂና የሚለው የግሪክ ቃል ምክንያትን የሚያሳይ ነው)።

የሐዋርያት ሥራ 2÷24-32 "እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፣ ሞት ይየዘው ዘንድ አልቻለምና" (ቊጥር 14) ይላል እንጂ፣ እግዚአብሔር ኢየሱስን እንደ ገና መንፈስ አድርጎ ሠራው አይልም። "ሞት ይይዘው ዘንድ ካልቻለ" የይሖዋ ምስክሮች ለምን ሞተ ቀረ ይሉናል?

ጴጥሮስ በመዝሙር 16÷8-11 ያለውን ቃል ከክርስቶስ ጋር ያያይዘዋል ሐዋርያት ሥራ 2÷25: 29-30 "…ደግሞ ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና… " (ቊጥር 26-27)። የሞተው የክርስቶስ አካል በሲኦል እንማይቀር "ተስፋ" ያደርጋል። በዚህ ቦታ ነፍስ የሚለው ቃል ሰብአዊ የሆነውን ሕይወት የሚያሳይ ነው (እነዚህን ክፍሎች ይመለከቷል ማቴዎስ 20÷28፤ ማርቆስ 10÷45፤ ዮሐንስ 10÷17-18። በእነዚህ ክፍሎች ላይ ነፍስ በግሪኩ ሱቼ የሚለው ቃል የክርስቶስን ሥጋዊ ሕይወት የሚያሳይ ነው)።

## 12. የሞተው አካል ነው ከሙታን የተነሣው

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሞተውን አካሉን ከሙታን እንደሚያስነሣ በዮሐንስ 2÷19-22 ላይ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ቊጥር 19 ላይ ይህን የሚለው አመልካች ቃል የሚያሳየው ኢየሱስ ቤተ መቅደስ ብሎ ስለሚጠራው አካሉ ነው። ይህም የሚያነገርበት ጊዜ የነበረው። ኢየሱስ አፍርሱት ቊጥር 19 ያለውን ነው ያስነሣው። የፈረሰው መንፈሳዊ አካል ወይም ቤተ ክርስቲያንን አይደለም። ነገረ ግን አካሉን ነበረ እንጂ የይሖዋ ምስክሮች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች አስነሣለሁ ያለው ቤተ ክርስቲያንን ነው የሚል አቋ አላቸው። ነገረ ግን ኢየሱስ አስነሣለሁ ያለው የፈረሰውን፣ በሦስተተኛውም ቀን የተነሣውን ነው።

ኢየሱስ፣ በሦሰት ቀን ያስነሣው አካሉን ነበረ እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አልነበረም። ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበተ ምዳራዊ ሕንፃ ው።

የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ሰዎች ያወቁት በተክለ ሰውነቱ ሳይሆን፣ በቅድመ ትንሣኤ ሕይወቱ የሚሠራውን ሥራ ደግሞ በመሥራቱ ነው፤ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድመ ትንሣኤ ሕይወቱ የነበረው አካል በድኅረ ትንሣኤ ሕይወቱ እንዳልነበረው

*የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ከሙታን የተነሣው መንፈስ ሆኖ ነው የሚል እምነት አላቸው።*

*በተወሰኑ አጋጣሚዎች ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ለምን በቶሎ አላወቁትም የሚለውን ጉዳይ በኋላ በስፋት የምንነጋገርበት ጉዳይ ቢሆንም፣ ሰዎች ኢየሱስን በማየት እርሱ መሆኑን ያወቁበትም ሁኔታ እንዳለ መዘንጋት አይኖርብንም* (ዮሐንስ 20÷16፤ *ማርያም ጀርባዋን ሰጥታ ቆማ ሳለ ኢየሱስ ስሟን በመጥራቱ ብቻ እንዳወቀችው እንመለከታለን*)።

*ኢየሱስ በስቅላቱ ወቅት በእግሮቹ፣ በእጆቹና በጐኑ የነበሩት ጠባሶች/እትራት ከትንሣኤውም በኋላ መኖራቸው የተሰቀለው አካል ራሱ ከሙታን እንደ ተነሣ የሚያስተምር ነው* (ዮሐንስ 20÷27-28)። *ቅዱሳት መጻሕፍት የሞተውና የተቀበረው ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሣ ማስተማራቸው፣ የሞተውና የተቀበረው አካል ራሱ እንደ ተነሣ የሚያስተምር ነው* (1ቆሮንቶስ 15÷3:4፤ *ሮሜ* 6÷3-5፤ *ቈላስይስ* 2÷12፤ *ሐዋርያት ሥራ* 2÷23-24፤ 3÷15፤ 4÷10፤ 5÷30፤ 10÷39-40፤ 13÷29-30)። *ኢየሱስ "ቤተ መቅደስ" ሲል ይጠራ የነበረውን ሥጋውን/አካሉን ከፈረሰ በኋላ በሦስተኛው ቀን ማስነሣቱ ያው የፈረሰው አካል ከሙታን እንደ ተነሣ የሚያስተምር ነው* (ዮሐንስ 2÷19)። *ኢየሱስ ሞቶ መነሣቱን ዮናስ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣ ዐንበሪ ኾድ ውስጥ ከመቆየቱ ጋር ማነጻጸሩ የሞተው አካል ራሱ ከሙታን እንደ ተነሣ በግልጽ የሚያስተምር ነው* (ማቴዎስ 12÷39-41)። *የክርስቲያኖች የትንሣኤ አካል ልክ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል እንደ ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል* (*ሐዋርያት ሥራ* 3÷15:26፤ 4÷2፤ *ፊልጵስዩስ* 3÷21)። *ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄን ክርስቲያኖች ባጽናናበት ክፍል ላይ፣ ጌታን አምነው የሞቱ ክርስቲያኖች ከጌታ ጋር ተመልሰው እንደ ሚመጡ እንዲሁም እንዲሁም በትንሣኤ አካል አብረውን እንደሚኖሩ ያስተማረው ትምህርት* (1ተሰሎንቄ 4÷13-18 ከ1ቆሮንቶስ 15÷18 *ጋር ያነጻጽሯል*) *የሞተው አካል ከሙታን እንደ ተነሣ የሚያስተምር ነው።*

## *13.* "ከሙታን መካከል" የሚለው ገለጻ የአካል ትንሣኤን ታሳቢ ያደረገ ነው

*"እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው"* (*ሐዋርያት ሥራ* 13÷30)። *"ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ"* (1 ቆሮንቶስ 15÷12) *የሚሉት ዐረፍተ ነገሮች ኢየሱስ ሌሎች ሞተው ከተቀበሩበት ስፍራ እርሱ ሕያው ሆኖ እንደ ተነሣ የሚያስተምር ነው። ይህ ደግሞ ትንሣኤው የአካል መሆኑን ታሳቢ ያደረገ ንግግር ነው። "ከ*[ἐκ] *ሙታን* [νεκρῶν]" *በሚለው ሐረግ ውስጥ "ኤክ" የሚለው የግሪክ ማስተዋድድ ከመቃብር "መውጣትን" የሚያሳይ ነው* (*አልዓዛር ከሞት ከመነሣቱ ጋር ያነጻጽሯል* ዮሐንስ 12÷1)።

## *14.* "ሞቼ ነበር፤ እነሆ አሁን ሕያው ነኝ" የሚለው አነጋገር ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው

*ሐዋርያት ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል የነሣ ጌታ እንደ ሆነ ማስተማራቸው ትንሣኤው የአካል ትንሣኤ መሆኑን የሚያጸና ነው* (*ሐዋርያት ሥራ* 13÷30-31፤ 17÷31፤ *ሮሜ* 1÷4 *በተለይ ራእይ* 1÷8 *ከዮሐንስ* 10÷18 *ጋር ያነጻጽሯል*)።

## 15. ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ በልቶአል

ኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤውን እውነተኛነት ለማስረገጥ ቢያንስ አራት ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር መግብ በልቶአል (ከኤማሁስ መንገደኞች ጋር ሉቃስ 24÷30፤ ከዐሥሩ ደቀ መዛሙርት ጋር ሉቃስ 24÷42-43፤ ከሰባቱ ደቀ መዛሙርት ጋር ዮሐንስ 21÷12-13፤ ከማረጉ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሙሉ ሐዋርያት ሥራ 1÷4)።

የክርስቶስ ትንሣኤ የአካል ትንሣኤ ነው የሚለው ሐቅ የማይዋጥላቸው ሰዎች፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ መብላቱ በአካል መነሣቱን የሚያስረግጥ ነው የሚለውን ድምዳሜ ላለመቀበል የሚያቀርቡት "ማስረጃ" በብሉይ ኪዳን በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ መላእክት ምግብ እንደ በሉ ተገልጾአል (ዘፍጥረት 18÷8፤ 19÷3)፤ መላእክት መናፍስት ሆነው ሳለ ምግብ መብላታቸው አካል አላቸው እንደማያሰኘው ሁሉ ኢየሱስም ከትንሣኤው በኋላ ምግብ መብላቱ ቊሳዊ አካል ወደሚለው ድምዳሜ አያደርስም ይላሉ። ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ መብላቱ መላእክት ምግብ ከመብላታቸው ጋር የማይነጻጸርባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ፤ ይኸውም፦ (1) መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት መናፍስት መሆናቸውን (ዕብራውያን 1÷14) በአንጻሩ ግን ኢየሱስ ሥጋና ዐጥንት እንዳለው (ሉቃስ 24÷39) በግልጽ ያስተምራል። መላእክት ለሰዎች ተገልጠው ምግብ መብላታቸው የእግዚአብሔርን ኪነ ጥበብ እንጂ፣ መላእክት እንደ ኢየሱስ ሥጋና ዐጥንት አላቸው ለማለት አይደለም። (2) መላእክት መናፍስት ናቸው፤ ኢየሱስ ግን እኔ መንፈስ አይደለሁም ብሏል (ሉቃስ 24÷39)። (3) ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምግብ የበላው እርሱ ራሱ ከሞት መነሣቱን ለማስረገጥ ሲሆን፣ መላእክት ግን ምግብ የበሉት እኛ ቊሳዊ ተፈጥሮ አለን ለማለት ፈልገው ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልእክት ለማስተላለፍ ብቻ ነው (ሉቃስ 24÷38-43)። በተለይ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ምግብ መብላቱና መጠታቱ እርሱ ራሱ በአካለ ሥጋ ለመነሣቱ ማረጋገጫ እንደ ሆነ ጴጥሮስ በግልጽ አስተምሮአል፣ ኢየሱስ "የታየውም ለሁሉም ሰው ሳይሆን፣ ከሙታን ከተነሣ በኋላ አብረነው ለበላንና ለጠጣን፣ እግዚአብሔርም አስቀድሞ ለመረጠን ለእኛ ለምስክሮቹ ነው" (ሐዋርያት ሥራ 10÷41)።

## ማጠቃለያ

እስካሁን ካየናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች በትክክል መረዳት የምንችለው ኢየሱስ በሞተበት አካሉ ከሙታን እንደተነሣ ነው። (1) መቃብሩ ባዶ መሆኑ፣ ቊሳዊው አካል ከመቃብር መውጣቱን የሚያስተምር ነው። (2) የትንሣኤው የዐይን እማኞች ክርስቶስን ከትንሣኤው በኋላ በንካታቸው፣ በጨበጣቸውና ማየታቸው የክርስቶስ ቊሳዊ አካል ሕያው እንደ ሆነ ያሳያል። (3) ክርስቶስ በእማማቱ ወቅት በአካሉ ላይ ከደረሰበት ሥቃይ የተነሣ በተለይም በእጆቹ፣ በእግሮቹና በጐኑ የነበሩት ቊስሎች ከትንሣኤውም በኋላ በነበረው አካል ላይ መታየታቸው ዐርብ ዕለት ሥቃይ የደረሰበት አካል ራሱ ከሙታን መነሣቱን ይፋ የሚያደርግ ነው። (5) ከትንሣኤው በኋላ የነበረው አካል ሥጋና ዐጥንት ያለው መሆኑ ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። (6) ኢየሱስ ምትሐት ያዩ የመሰላቸውን ደቀ መዛሙርት ልብ ለማጽናት ምግብ አብሮአቸው መብላቱ ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ የሚያስረግጥ ነው። (7) ከትንሣኤው በኋላ የነበረው አካል "ሶማ" ተብሎ መጠራቱ ቊሳዊ አካል እንደ ሆነ የሚያስተምር ነው። (8) በርካታ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ኢየሱስ ሞተ፣ ተቀበረ፣ ከሙታን ተነሣ የሚለው ገለጻቸው የሞተው፣ የተቀበረውና ከሙታን የተነሣው አካል አንድ እንደ ሆነ የሚገልጽ ነው። (9) "ከሙታን መካከል" የሚለው ገለጻ ኢየሱስን ሞተው በመቃብር ውስጥ ካሉት ሰዎች ጋር የሚያነጻጽር መሆኑ ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ የሚያስረዳ ነው። (10) "ኢየሱስ ሞቶ ነበር እነሆ አሁን ሕያው ነኝ" የሚለው ንግግሩ፣ የሞተው አካል ከሙታን

እንደ ተነሣ የሚያሳይ ነው፡፡ (11) ኢየሱስ አይሁድ የሚያፈርሱትን አካል ከሙታን እንደሚያስነሣ ትንቢት መናገሩ ትንሣኤው የአካል እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ (12) የሐዲስ ኪዳን ፀሓፍያንም ሆኑ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ትንሣኤ ሙታን የአካል እንደ ሆነ በግልጽ ማስተማራቸው የኢየሱስ ትንሣኤ የመንፈስ እንድንል አያደርገንም፡፡ (13) ቅዱሳት መጻሕፍት ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ሰው ሆኖ እንዳለ እንዲሁም ተመልሶ እንደሚመጣ ማስተማራቸው ትንሣኤው የአካል መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡ (14) ትንሣኤ የሚለው ቃል የሞተ ነገር በጊዜያዊነትም ሆነ በኋሚነት ከሙታን መነሣቱን የሚያመለክት መሆኑ ትንሣኤው የአካል መሆኑን የሚያስተምር ነው፡፡ ለዚህም ነው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመት በሃይማኖት መግለጫዋ ላይ፣ በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ የሚለውን እምነቷን ይፋ ስታደርግ ይህንንም እውነት ስትሰብክና ያመኑትንም ደቀ መዛሙርት ይሆኑ ዘንድ ስታጠምቅ የኖረችው፡፡